MCPS QuickNotes

## በ2015 የበጀት አመት የስራ ማስኬጃ በጀት ህዝባዊ ስብሰባ ይገኙ

የበላይ ተቆጣጣሪ ጆሹዋ ስታር ለ2015 (በጀት አመት) የ2.28 ቢልዮን የስራ ማስኬጃ በጀት በዲሴም. 10 ለትምህርት ቦርድ ረቂቁን አቅርቧል። የዶ/ር ስታር ረቂቅ፣ የስኬት ክፍተትን የማጥበብ ጥረትን ዳግመኛ ሃይል ለመስጠት እና የMCPS ሰራተኞችንና ተማሪዎችን ለወደፊት እድሎች ለማዘጋጀት የሙአለ ንዋይ ፈሰስ እያደረገ፣ ዲስትሪክቱ ቀጣዩን የምዝገባ እድገት መቋቋሙን እንዲቀጥል ያስችለዋል። ስለ ዶ/ር ስታር በጀት ረቂቅ ይበልጥ ለመማር የMCPS Operating Budget (የስራ ማስኬጃ በጀት) ድር ገፅ ይጎብኙ። እናም በሚመጡት ሁለት ህዝባዊ ስብሰባዎች በበጀቱ ረቂቅ ያለዎትን ሀሳብና አስተያየት ለማጋራት አይጠራጠሩ፡- የመጀመርያው **ሀሙስ ጃንዩ.** 9 በ7 p.m፣ ሁለተኛው ደግሞ **ሀሙስ ጃንዩ.** 9 በ7 p.m ናቸው። ሁለቱም ስብሰባዎች የሚካሄዱት በCarver Educational Services Center, 850 Hungerford Drive, Rockville በሚገኘው አዳራሽ ነው። ከስብሰባዎቹ ባንዱ ለመናገር ከሰኞ ዲሴም. 16 ጀምሮ መመዝገብ ይችላሉ።

ቦርዱ በተጨማሪ **ማክሰኞ ጃንዩ.** 21 እና **ሀሙስ ጃንዩ.** 23 ሁለት የበጀት ስራ ስብሰባዎችን ይመራል። እነዚህ ስብሰባዎች ለህዝብ ክፍት ናቸው። **ማክሰኞ ፌብሩ.** 11፣ ቦርዱ ለካውንቲው ስራ አመራርና ለካውንቲው ምክር ቤት ለግንዛቤ የሚቀርብ በጀት እንዲያፀድቅ ይጠበቃል።

## በመቃረብ ላይ፡- 17ኛው አመታዊ የላቀ አገልግሎት ሽልማቶች ለህዝባዊ ትምህርት

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ ለ17ኛው አመታዊ የላቀ አገልግሎት ሽልማቶች ለህዝባዊ ትምህርት ብቁ የሚሆኑ ሰዎች ስያሜ በመጠበቅ ላይ ይገኛል። በMontgomery County ለህዝባዊ ትምህርት የላቀ አስተዋፅኦ ላደረጉ ግለሰቦች (ተማሪዎችን ጨምሮ)፣ ቡድኖች፣ እና ድርጅቶች እውቅና ለመስጠትና አድናቆት ለማሳየት ሽልማቶቹ የሚመሩት በቦርዱ ነው።

የእጬዎች መሰየሚያ ፎርሞች በዲሰምበር ወር በትምህርት ቦርድ ድር ጣብያ ይገኛሉ። የተሞሉ ፎርሞች በፌብሩዋሪ ገቢ እንዲሆኑ ይጠበቃል። በቀጣይ የQuickNotes ህትመቶች ተጨማሪ መርጃዎች ይሰጣሉ።

## ለስቴት ሽልማት አንድ ወላጅ ሰይሙ

የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምርያ (MSDE) ለሜሪላንድ አመታዊ የወላጅ ተሳትፎ ጉዳዮች ሽልማት (Maryland Parent Involvement Matters Award) (PIMA) እጬዎች ስያሜ በመፈለግ ላይ ነው።

ሽልማቱ በህዝባዊ ት/ቤቶች የወላጅ ተሳትፎ አስፈላጊነትን እውቅና ይሰጣል። የሜሪላንድ አመታዊ የወላጅ ተሳትፎ ሽልማት ተሰያሚዎች የሜሪላንድ ህዝባዊ ት/ቤት የሚማሩ ልጆች ወላጆች ወይም ህጋዊ ጠባቂዎች መሆን አለባቸው፣ የMSDE ወይም ያካባቢ ት/ቤት ስርአትተቀጣሪዎች መሆን የለባቸውም። የማመልከቻ የግዜ ገደብ **አርብ ጃንዩ. 31** ነው። ለተጨማሪ መረጃ የ[MSDE ድር ጣብያ ]ጎብኙ።

**በዊንተር እረፍት የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሰአታት አግኙ**

የዊንተር እረፍት ተማሪዎች በአገልግሎት እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉና የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ሰአቶች ለማግኘት ከፍተኛ ግዜ ነው። ተማሪዎች በተለያዩ እንቅስቃሴዎች መሳተፍ ይችላሉ፡— በሱፕ ኪችን (ለድሆች በነፃ ምግብ የሚሰጥበት) ለመስራት፣ ያካባቢ መናፈሻ ቦታ ማፅዳት፣ ወይም ለችሮታ ልብስ ወይም ምግብ ማሰባሰብ። ሁሉም የMCPS ተማሪዎች ከ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ለመመረቅ 75 የSSL ሰአቶች ያስፈልጓቸዋል።

[ለSSL ሰአቶች የፀደቁ ] ድርጅቶችንና እድሎችን ፈልጋችሁ አረጋግጡ። በተጨማሪ፣ በመጀመርያው ግማሽ አመት የተከናወኑ የአገልግሎት ሰአቶች ከ**አርብ ጃንዩ. 3** በፊት ለት/ቤቱ የSSL አስተባባሪ ገቢ መሆን እንዳለባቸው አስታውሱ።

[የተማሪ አገልግሎት ትምህርት]

**በMLK ያገልግሎት ቀን የት ታገለግላለህ/ታገለግያለሽ?**

ሰኞ ጃንዩ. 20 Montgomery County የDr. Martin Luther King, Jr (ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁር.) ያገልግሎት ቀን ያከብራል። ባገር አቀፍ ደረጃ የዶ/ር ኪንግን ህይወትና ተግባር የሚዘክረው ብሄራዊ በአልን ለማክበር ማህበረሰባቸውን የሚያገለግሉትን በሺዎች የሚቆጠሩ አሜሪካውያንን ተቀላቀሉ።

ከቤተሰብና ጓደኞች ጋር በመሆን ዋጋ/ክብር ባላቸው እንቅስቃሴዎች እየተሳተፉ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሰአቶች ማግኘት ለተማሪዎች ከፍተኛ እድል ነው። የአገልግሎት ፕሮጀክቶች በካንቲው የተለያዩ ሶስት ቦታዎች ላይ ይከናወናሉ፡-

Bethesda North Marriott Conference: 1– 3 p.m.
Silver Spring Civic Center: 10 a.m. – እኩለቀን
Universities at Shady Grove: 10 a.m. – እኩለቀን

ለአካባቢ መጠለያዎች ሳንድዊቾች መስራት፣ ለአዛውንቶችና አርበኞች ካርዶች ማጌጥ፣ እና ግላዊ እንክብካቤ እሽጎች ማሰባሰብ በመሳሰሉ ነጠላ ፕሮጀክቶች ላይ እና/ወይም ቡድን ፕሮጀክቶች ላይ ፈቃደኞች መስራት ይችላሉ።

ለተጨማሪ መረጃዎች [Montgomery Serves (ሞንትጎመሪ ያገለግላል) ድር ጣብያ] ጎብኙ ወይም 240-777-2600 ይደውሉ።

**የሚቀጥለው ተማሪ የቦርድ አባል ማን ይሆናል?**

በ2014-2015 የትምህርት አመት የትምህርት ቦርድ አባል (SMOB) ሆነው ለማገልገል የሚፈልጉ የሶፎሞርና የጁንየር ተማሪዎች ማመልከቻዎች አሉ። የማማልከቻ ማቅረቢያ የግዜ ገደብ **ሀሙስ ጃንዩ. 23** በ 4 p.m. ነው። SMOB በትምህርታዊ ጉዳዮች የአስተዋይ ተማሪ አስተያየት ይሰጣል። SMOB ህግ መፃፍ ይችላል፣ በሁሉም አርእስቶች በሚካሄዱ ውይይቶች ይካፈላል እናም ባንዳንድ ጉድዮች ድምጽ የመስጠት መብት አለው።

የSMOB የስራ መደብ  አይከፈልም፣ ነገር  ግን የተማሪ አባል የማህበራዊ ጥናቶች ክሬዲት ያገኛል፣ ቢያንስ 250 የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ሰአቶች፣ እናም $5,000 የኮሌጅ ስኮላርሺፕ ይቀበላል።

ይፋ ያልሆነ ስብሰባ **ማክሰኞ ጃንዩ. 7**፣ 5-6 p.m. በተማሪዎች ጉዳይ ፅ/ቤት 12900 Middlebrook Road, Germantown ይከናወናል። ያሁኑ ተማሪ አባል፣ ጀስቲን ኪም (Justin Kim)፣ እንዲሁም የቀድሞዎቹ SMOBዎች፣ አስተያየት ለመስጠትና ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት በቦታው ይገኛሉ።

ለቦታው ብቁ ለመሆን፣ ተማሪዎች ተቀማጭነታቸው Montgomery County መሆን አለበት እናም በ2ኛ ደረጃ ት/ቤት የሶፎሞር ወይም የጁንየር ተማሪ ሆነው የተመዘገቡ መሆን አለባቸው።

ለተጨማሪ መረጃ Karen_L_Crawford@mcpsmd.orgን ይገናኙ።

ተጨማሪ መረጃ

**እንዳይረሱ...**

የኤሌሜንታሪ ማእከል ፕሮግራሞች ለከፍተኛ ተሰጥኦ ላላቸው  ለ4ኛና ለ5ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚያበለፅግ፣ የሚያፋጥንና የMCPS ስርአተ ትምህርት የሚያስፋፋ የትምህርት አካባቢ ያቀርባል። የከፍተኛ ተሰጥኦ ያላቸውና ለተነሳሱ/ለተነቃቁ ተማሪዎች በሂሳብ፣ በቋንቋ ስነጥበባት፣ በሳይንስና በማህበራዊ ጥናቶች ፍላጎታቸውን ለሚሟላት የተተለመ ነው። ፕሮግራሙ የሚያተኩረው በሂሳዊ አስተሳሰብ ችሎታዎች፣ ፕሮብሌ-አፈታት ችሎታዎች፣ እና በመገናኛ ችሎታዎች ነው።

ለከፍተኛ ተሰጥኦ ላላቸው የኤሌሜንታሪ ማእከል ፕሮግራሞች ማመልከቻ አሟልተው ላቀረቡ ተማሪዎች በጃኑዋሪ በየአካባቢ ት/ቤቶች ፈተና ይሰጣል።

ተጨማሪ መረጃ

**ያስታውሱ ...**

የት/ቤት መጀመርያና መጨረሻ ሰአቶች ላይ በቀረቡት ለውጦች ከሚከናወኑት አራት የማህበረሰብ ስብሰባዎች ሁለተኛው ሰኞ ዲሴምበር 16 በ7 p.m.-8:30 p.m Richard Montgomery High School, 250

Richard Montgomery Drive, Rockville ይከናወናል። ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ እና የማህበረሰብ አባላት ስለቀረቡት ለውጦች አስተዋፅኦ ለማድረግና ጥያቄዎች ለማቅረብ እድል ይኖራቸዋል።

የማህበረሰብ መድረኮች የMCPS የበላይ ተቆጣጣሪው ለደወል ሰአቶች ስላቀረበው ረቂቅ አስተዋፅኦ የሚያሰባስብበት አንዱ መንገድ ናቸው። ለተጨማሪ መረጃ የMCPSን ድር ጣብያ ይጎብኙ።

[የደወል ሰአቶች]

**እንዲሁም...**

**ያገለገለ መኪና ወይም ኮምፒውተር በማፈላለግ ላይ ካላችሁ፣ ዲሴም. 14 የሚካሄደው የ**Automotive Trades (ATF) እና የInformation Technology (ITF) **በጎ አድራጎቶች የመኪናና የኮምፒውተር ሽያጭ አያምልጣችሁ!**

በATF እና በITF የሚገኙ ተማሪዎች ያደሷቸውን ያገለገሉ መኪኖችና ኮምፒውተሮች **ቅዳሜ ዲሴም. 14** Damascus High School፣ ከ9-11 a.m. ይሸጣሉ።

ለሽያጭ ስለሚቀርቡ መኪናዎች ተጨማሪ መረጃ ኬሊ ጆንሰንን (Kelly Johnson) በ301-929-2197 ይጠይቁ፣ ወይም [www.atfcareers.org] ጎብኙ። ለሽያጭ ስለሚቀርቡ ኮምፒውተሮች ተጨማሪ መረጃ፣ [www.itfcareers.org] ጎብኙ

መኪኖቹና ኮምፒውተሮቹ የታደሱትና የተፈተሹት የመማርያ ክፍልና የላቦራቶሪ አካል በመሆን በተማሪዎች ነው።

የማህበረሰብ አባላት ለፕሮግራሙ ተሽከርካሪዎች እንዲሰጡ ተጋብዘዋል። መኪኖችን የautomotive ፕሮግራም ባላቸው በDamascus፣ Gaithersburg፣ Seneca Valley ወይም Thomas Edison የ2ኛ ደረጃ ትም/ቤቶች መስጠት ይቻላል። ስጦታዎ ከአገርውስጥ ገቢ ታክስ ቅነሳ ሊታሰብ ይችላል።

[Automotive Trades Foundation]
[(የአውቶሞቢሎች ንግድ ስራ ተቋም)]
[Information Technology Foundation, Inc.]
[(የመረጃ ቴክኖሎጂ ተቋም የንግድ ማህበር)]

**የህትመት ፕሮግራም ...**

MCPS QuickNotes በዊንተር እረፍት ወቅት አይታተምም፣ ስለዚህ የሚቀጥለውን ህትመት ማክሰኞ ጃኑዋሪ 7 ተጠባበቁ። እስከዚያው፣ ስለMontgomery Count ህዝባዊ ት/ቤቶች ወቅታዊ ዜናና መረጃ ለመከታተል አይናችሁን [MCPS ድር ጣብያ] እና [Twitter] ላይ ጣሉ።